# ኢየሱስ ማን ነው?

‘ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፣ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን።’

2ኛ ቆሮንቶስ 4፥5

*ፓኦል ዎከር*

2017

ይህን ቡክሌት ለእናንተ፤ ለአንባቢያን አበርክቼላቹኋለሁ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ላካፍላቹሁ ስለፈቀዳቹሉኝ አመሰግናለሁ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምንም ዓይነት መደበኛ መመሪያ የለኝም፤ በብዙ ሥነ–መለኮታዊ ጉዳዮች ላይም አቋሜ ግልጽ አይደለም። እኔ ግን የኢየሱስ ተከታይ ነኝ፤ እና ቅዱሳት መጻሕፍትን እወዳለሁ። አንዳንድ ሀሳቦችን እንዳካፍላቹሁ ፍቀዱሉኝ፡-

## መግቢያ፥

**ይህን ጥያቄ እየጠየቃቹሁ ከሆኑ፡- 'ኢየሱስ ማነው?'፡- በእውነት አስደናቂ ሁኔታ ላይ ናቹሁ!**

በአምላክ ላይ ልትቆጡ ትችላላቹ፣ ወይም አሁን በእግዚአብሔር አታምኑም። ወይም ምናልባት በእግዚአብሔር ታምናላቹ ነገር ግን ተጎድታቿል። ምናልባት የእስልምና፣ የሂንዱ፣ የቡዲስት ወይም የሌላ እምነት ተከታይ ልትሆኑ ትችላላቹ። በአጠቃላይ እራሳቹን መግለፅ እማትችሉበት የተለየ ሁኔታ ላይ ልትሆኑ ትችላላቹ፡- ምንም ይሁን ምን ወዳጆቼ፣ ያላቹበት ስሜት ወይም ያላቹበት ሁኔታ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አምላክ፡- ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው መጽሐፍ ያድማቿል፣ በተጨማሪ ' **'ኢየሱስ ማን ነው?'** ብላቹ እንድትጠይቁ ይማጸናቿል።

የማትችሏቸው እና መብትሄ ያጣቹለት ብዙ ጥያቄዎች ሊኖሯቹ ይችላሉ። በእውነት፣ በዚህች አጭር ቡክሌት ውስጥ፣ ወደ እናንተ የመጣሁት በኢየሱስ 'አማኝ' ሆኜ ብቻ ነው፣ እና በቀላሉ አንዳንድ ሃሳቦችን ላካፍላቹ። የእምነቴ ምንጮቼ፤ መጽሐፍ ቅዱስ፤ እና የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ፡- 66ቱ 'መጽሐፍት' ወይም ጽሑፎች የተቀናበረው፡- በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አምናለሁ። እንደማንኛውም ጥሩ ወይም 'እውነተኛ' ነገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ በተሳሳተ መንገድ ልናውቀው፣ ልንጠቀምበት እና ልንትጠራጠረው እንችላለን። ይሁን

እንጂ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሲጠቀሙ ጉድለቶች ቢኖሩትም፣ እውነትን ለሚፈልግ ታማኝ የአምላክ ምንጭ ሆኖ ይቀጥላል። ለማንበብ ቀላል ይሆን ዘንድ፣ በ‘ያልተማሩ’ ሰዎች ነው የትጻፈው። እግዚአብሔር ራሱን ከእኛ በመጽሐፍ ቅዱስ አልሰወረም፤ እንዲያውም ራሱን ገልጦልናል!

**‘ኢየሱስ ማነው?’** ለሚለው በጣም አስፈላጊ ጥያቄ አሁን ዘልዬ ልግባና ሃሳቤን ላቀርብላቹሁ።

# ኢየሱስ ማን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ትርጉሙም 'ጌታ ያድናል':- አምላክ በሰው አምሳል መሆኑን ያስተምረናል። እግዚአብሔርን ‘በግላችን’ እንድናውቀው እና ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ በሙሉ እንድንገናኝ፣ እግዚአብሔር ሰው ለመሆን ከሰማይ ወረደ።

ኢየሱስ ‛በሥጋ’ አምላክ ነው። እርሱ የመጣው ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን እና የዘላለም ሕይወትን ሊሰጠን ነው። ግን ይህ ኢየሱስ ‛ማን ነው’ እና ‛ለምንስ’ መጣ።

## ራዕይ፥

ይህ የማይመረመር፣ ለመረዳት የማይቻል እውነት እንደሆነ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ወደ ሰው መልክ መቀየሩ፤ እኛ በቀላሉ ይህንን እውነት ‘መረዳት’ አንችልም። ይህንን 'መረዳት' አንችልም! ለእኛ ከአቅማችን በላይ ነው! አዎን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እውነት፡- እንደዚህ ያለ አስደናቂ እውነት፡- አእምሯችን እንዲሸከመው ተደርጎ እንዳልተፈጠረ ይነግረናል!

ይህ የእግዚአብሔር እውነት፡- ኢየሱስ ክርስቶስ፤ 'መንፈስ እና እውነት' እንደሆነ ተነግሮናል፣ እና ወደ እኛ የሚመጣው አእምሮን 'በማስተዋል' ሳይሆን፣ በመንፈሳችን፣ በልባችን 'መገለጥ' ነው።

እናንተ፡- እንደ እኔ እና እንደ ብዙዎቹ እግዚአብሔርን 'ለመረዳት'ወይም እሱን በአእምሮአን ላይ ለማስፈር ከሞከርን፣ መንፈሳችን እና ልባችን እንዲመሩን መፍቀድ በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ታውቃላቹ ወዳጆቹ ሆይ፣ አሁን በህይወታቹ ውድ የሆነ ነገር ሁሉ፡- ጓደኞች፣ ቤተሰብ፣ ደስታ፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ ይቅርታ፣ ምህረት፡- እነዚህ ነገሮች የአዕምሮ ‘እውነታ’ ሳይሆኑ የልብ እና የመንፈስ ናቸው። እንዲያውም፣ ብዙ ጊዜ፤ አእምሯችንን፣ መረዳታችንን፣ ‘የልብ እውነት’ን ወይም ግንኙነቶቻችንን እንዲጎዳ እናደርገናል።
**‘ጭንቅላታቹን’ ልባቹን እንዲቆጣጠር ፈቅዳቹ ታውቃላቹ፣ በመፍቀዳቹስ ተጸጽታቹ ታውቃላቹ?** እግዚአብሔር በትንሿ አእምሮዬ ወይም በዘፈቀደ 'ግንዛቤ' ውስጥ 'የሚስማማ' ከሆነ፣ እርሱ በጣም ትንሽ አምላክ ነው፣ በእርግጥ!

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‘እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ አምላኪዎቹም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል’ ተብሎ ተነግሯል። ኢየሱስ ራሱ ስለ ቃላቱና ስለ መገለጡ ‘ቃሌ መንፈስና ሕይወት ነው’ ብሏል።

**የኢየሱስ እውነት/ሃቅ ለአእምሯችን ፈታኝ ነገር ነው፣ ግን የልባችን በር እንደማንኳኳት ተሰምቷቹ ያውቃልን?**

*<u>የክርስቶስ መልእክ፥</u>*

ኢየሱስ ሰዎችን፣ ‘ለእምነታቸው’ እንዴት እንደተናገረ ትኩረት የሚስብ ነው። ገንዘብ ወይም ሀብት እየሰጠ አልመጣም። ለሥነ መለኮት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እንኳን አልመጣም። እንዲህ አለ፡– ‘የተጠማ አለ? ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፡– በእኔ የሚያምን ሁሉ በውስጣቸው የሕይወት ውኃ ምንጭ ይፈሳል።” ኢየሱስ፤ 'ተጠምተን' እንደሆነ ጠየቀን እና 'የሕይወት ውሃ' ቃል ገባልን። ይህ ለእለት ኑሯችን ወይ ለአእምሯችን 'አይመጥንም'፤ ነገር ግን ወደ ነፍሳችን ጠልቆ ይወርዳል እና ተጨማሪ ነገር ፍላጎቶቻችንን የሚያሟላ ይመስላል።

**‘ተጠምትሃልን?' ብሎ ኢየሱስ የጠየቀው ጥያቄ፣ በነፍሳቹ ያስተጋባልን?**

ወይም ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ወደ ሕዝቡ ዞር ብሎ ‘የደከመ አለ?’ ብሎ ጠየቀ፣ ከዚያም የተለየ ዓይነት ‘ዕረፍት’ ቃል ገባልን።

ኢየሱስ ተአምራትን አድርጓል፣ ነገር ግን ለተአምራቱ የተለየ ዓላማ ነበረው። አንድ ጊዜ ኢየሱስ ተአምራትን ያደረገበት ምክንያት ኃጢአትን ይቅር የማለት ኃይል እንዳለው ሁላችንም እንድንረዳ በዙ ሰዎች ፊት ተናገረ። ለአጭር ጊዜ ሕይወትን ለማሻሻል ሲል ብቻ ተአምር አልሰራም።ኃጢአታችንን ይቅር የማለት ኃይሉን እንድናይና ‘ስማችንን በመንግስተ-በሰማይ እንድንጽፍ’ ተአምራት አድርጓል።

## ታዲያ መልእክቱ ምን ነበር? በነፍሴ ውስጥ ይህን የ'ሕይወት ዕረፍት'፣ እነዚህን 'የሕይወት ውኃዎች'፣ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የኢየሱስ መልእክት ህይወት የሚዘራበት፤ በጥሬው ግልጽ የሚሆንበት በሚከትለው ላካፍላቹ፡-

ኢየሱስ 'በሩ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ይድናል' ብሏል። ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንድናውቅ ወደ ራሱ ጋበዘን። አሁን በህይወታቹ ውስጥ ያላቹ ጥልቅ ነገር ቢኖር 'አንድ ሰው' ነው እንጂ፣ የሆነ ነገር ወይም አንዳንድ ጽንሰ-ሀሳብ አይደለም። እስኪ ለአንድ ደቂቃ ያህል አስቡበት።

**በስተመጨረሻስ በጣም እንቁ ነገር ቢኖረኝ እምትሉት ምንድነው?** ሰው መሆኑን አረጋግጥላቿለሁ። እግዚአብሔር አንድ ነው። ለእናንተ ጥልቅ የሆነው የእግዚአብሔር እውነት፡- ራሱ መሆኑ ነው። ሰው ሆኖ የማሳየቱ አላማ እኔ እና አንተን እሱን ለማየት፣ ለመዳሰስ እና እንድናውቀው ነው። እንዲያውም፣ አንድ ስም ኢየሱስ የተሰጠው 'አማኑኤል' ሲሆን ትርጉሙም 'እግዚአብሔር ከእኛ ጋር' ማለት ነው። ኢየሱስ፡- እግዚአብሔር እንደ ሰው፡- የመጣው ዛሬ እና ለዘላለም ከእኛ ጋር እንዲሆን ነው።

## እግዚአብሔርን በግል ማወቅ ትፈልጋላቹን?

## <u>እምነት፥</u>

ኢየሱስ ‘በእርሱ እንድናምን’ አጥብቆ ይማጸነናል። እሱ በእርግጥ ከሰዎች ጋር በነበረበት ጊዜ ይህ የእሱ ግብግብ ነበር፤ እነሱም ‘እያዩት’ ነበር። እሱን ‘ማየት’ ከቻሉ፣ እሱን ‘ማመን’ ላይ ይህ ሁሉ ትኩረት ለምን አስፈለገ? በዚህ የእምነት ጉዳይ ላይ ሁለት ነገሮች ተገልጠውልኛል፡–

1. **እውነተኛ ጓደኛ በአንተ ያምናል!**

ለናንተ ያልሆነ ሰው ነገር ግን ጓደኛ የምትሉት ሰው ኑሯቹሁ አታውቁምን? እነኝህ ሰዎች የማያውቃቹሁ፣ እና በዙሪያቸው መኖራቹሁንም ዋጋ የማይሰጡ ናቸው። እነዚ ሰዎች ከናንተ ጋር ከፍ ያለ ግንኙነት ቢኖራቸውም፣ እምነታቸውን አይጥልባችሁም። የተወሰነ ልባቸውን ዘግተውባችኋል። **ይህ ስሜት በ ወዳጅነት ውስጥ ተሰምቷቹ ያውቃልን?**

ኢየሱስ መጣ፡– እግዚአብሔር በሥጋ፡– 'ከእኛ ጋር' ሊሆን። ኢማኑኤል የሚለው ስሙ ራሱ ‘አምላክ ከእኛ ጋር’ ማለት ነው። ከእኛ ጋር ፍቅር፣ ‘እምነት’፣ ግንኙነት እንዲኖረው መጣ። <u>እርስ በርሳችን መተማመን የእውነተኛ ወዳጅነት ደም ነው።</u>

ኢየሱስም፤ ‘ወዳጄ ብያችኋለሁ’ አለ።

ኢየሱስም ጓደኛ፣ ነፍሱን ለወዳጁ ከመስጠት የበለጠ ፍቅሩን ማሳየት የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ተናግሯል።

## 2. ማየት ማመን አይደለም!

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ኃይሉን አይተው ነበር፣ ነገር ግን በእሱ አላመኑም። ምናልባት እናንተም፣ እንደ እኔ፣ አንዳንድ ጊዜ ትመኙ ወይም እንዲያውም፣ “ምነው ኢየሱስን ‘ማየት’ በቻልኩ ትሉ ይሆን’፤ እውነቱን ነው፣ ብዙዎች፡– አብዛኞቹ፡– በሥጋ ያዩትና ተአምራዊ ኃይሉን የመሰከሩት፣ በእርሱ አላመኑም። ብዙ ጊዜ፣ እንዲያውም፣ ተአምራትን ሲሰራ፣ ሰዎች በእርግጥ ተቃወሙት። በመጨረሻም ‘ያዩት’ ሁሉ፡– እሱን የሰሙት፣ አብረውት የሄዱትም፣ በምልክቶቹና በድንቅ ነገሮች የተደሰቱም፡– በስተመጨራሽ በእሱ ላይ ሴራ ሰሩ የተወሰኑቱም ጣሉት። እርሱን ‘ባዩት’ ሁሉ በፊታቸው በማለዳ ብርሃን ተገደለ።

ስለዚህ ኢየሱስ የጠራን ወደ ‘ማምን’፣ ወደ ‘እምነት’ እንጂ ወደ ‘ማየት’ አይደለም። ሰው ባየው ጊዜ ገደለው። በአይናችን የምናየውን ለመከተል እና ታማኝ ለመሆን እራሳችንን ማመን አንችልም። እንደ ደቀ መዛሙርቱ ለተወሰነ ጊዜ ታማኝ እንሆን ይሆናል፣ ነገር ግን በሆነ ጊዜ ዓይኖቻችን፣ አእምሯችን፣ ልባችን ያዋርዱናል እና እኛ አንከተልም።

ያየነውንና በአንድ ወቅት የምንወደውን እንቃወም ይሆናል።

ኢየሱስ ደቀ መዝሙሩን ቶማስን፤ ‘ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው’ አለው።

እዚህ ምድር ላይ፣ ኢየሱስ በልባችን አይን ‘እንድናይ’ እና እንድናምን ይፈልጋል፡- ማለትም እንድንቀበል፣ እንድንከተል፣ እንድንታዘዝ፣ እንድናመልክ። ኢየሱስ ከእናንተ ጋር እውነተኛ ግንኙነት፣ ጓደኝነት ይፈልጋል! አንድ ቀን ወደ ክብር እንሸጋገራለን፣ ዓይኖቻችን ንጹህ ይሆናሉ፣ ልባችንም ጸንቶ ይኖራል፣ እና እሱን 'ፊት ለፊት' እናየዋለን። አሁን ግን ጥሪው እንድናምን ነው።

**ኢየሱስን ብልብ ዓይናቹ እያያቹሁ እንደሆነ ይሰማቿል?**

## ውድ ሀብት፥

**ኢየሱስን ‘ለማየት’ እና ለማመን የሚከብደው ለምንድን ነው? አለም ሁሉ ስለ ኢየሱስ ሰምቶ የማያምን ለምንድነው?**

መጽሐፍ ቅዱስን ሳነብ፣ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ አስገርሞኛል። ከጥንት ጀምሮ፣ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በእኩልነት ቢወድም፣ አንዳንዶች እግዚአብሔርን ‘አወቁ’፣ አንዳንዶቹ ግን አላወቁም። ይህም፡- ለእንኛ፤ ለመረዳትም፤ ለማብራራትም የማይቻል ነው።

ኢየሱስ በምድር ላይ ሲመላለስ፣ ሲሰብክ እና ተአምራትን ሲያደርግ ተመሳሳይ ነበር። አንዳንድ ሰዎች በእግሩ ሥር ወደቁና ‘አንተ ጌታ ነህ!’ አሉ፣ ሌሎች ደግሞ ንቀውት፣ ሥልጣኑን ተቃወሙት። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? አንድ ሰው ክርስቶስን አይቶ እግዚአብሔርን ያያል። ሌላው ደግሞ ክርስቶስን በተመሳሳይ ጊዜ አይቶ ሰውን ብቻ ያያልን? ይህንን ማብራራት አልችልም!

ነገር ግን በኢየሱስ ህይወት እና ትምህርት ያየሁት ነገር እራሱን በጥልቅ እና በጸጥታ መንገድ መግለጡን ነው። በጣም በጥልቀት እና በጸጥታ! አንድ ሰው በእውነት ኢየሱስን ስለ ማንነቱ 'ባየው'፡- 'እግዚአብሔር ከእኛ ጋር'፡- መገለጡ በሰውየው ልብ ውስጥ ደረሰ እና ለዘላለም ቀየረው። ነገር ግን ይህ መገለጥ ጥልቅ እና ንፁህ እና ጸጥታ የሰፈነበት ስለሆነ፣ አብዛኞቻችንን ሳናስተውል ያልፋል። በሕይወታችን ፊት ላይ ባለው ብዙ ጫጫታ እና

ምኞት ሃሳባችን ተከፋፍሏል፣ የእግዚአብሔርን ወሳኝ ነገሮች ስንጠቀምባቸው ያልፉናል።

ኢየሱስ ይህን እውነት ለማስረዳት በጣም አጭር ምሳሌ ተናግሯል። እንዲህም አለ፡– ‘መንግሥተ ሰማያት በመሬት ውስጥ የተቀበረ የማእድን ሀብት ትመስላለች። አንድ ሰው ባገኘው ጊዜ እንደገና ሸሸገው፤ ከዚያም በደስታው ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጦ፤ ያንን ማእድን ገዛው።

**በዙሪያቹሁ ያሉ ብዙ ሰዎች ማየት ያአልቻሉትን፤ እናንተ ግን ኢየሱስ ውድ ሀብት እንደሆነ ማየት እንደጀመራቹሁ ይሰማችዋልን?**

**ደም፥**

የኢየሱስ ታሪክ አስደናቂ ነው! አምላክ እንደመሆኑ መጠን ከኃጢአታችን፣ 'ከእድፍታችን' ነፃ ሊያወጣን እንደመጣ ተነግሮናል። ታውቃላችሁ፣ የኃጢአታችን ጥልቅነት አብዛኛውን ጊዜ የደም ፈለግ ይተወዋል። የሰው ሕይወት ምንጭ የሆነው ደም፣ ዓመጽ ባለበት፣ በደል ባለበት፣ መጥፎ ዕድል ባለበት፣ ሞት ባለበት ይፈሳል። ሁላችንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እጃችን አለበት። የምንኖረው በባርነት እና በበደል ላይ በተገነባ ዓለም ውስጥ ሲሆን፤ ሁላችንም ወይ ደም አፍስሰናል ወይም የሰዎችን ደም ዋጋ ያስከፈለውን የተሰረቀ ንብረት ተጠቅመናል። ይህ ግልጽ እና የማይመችን ሃቅ፥ ነገር ግን ደም መፋሰስ የዓለማችን ጨለማ እና ከእግዚአብሔር የመለየታችን ዋና አካል ነው።

ስለዚህ ኢየሱስ ይመጣል፤ እናም እኛን ከዚህ ኃጢአት እና ጨለማ ነፃ ሊያወጣን ይፈልጋል። ከደረሰብን በደል፣ ከበደልንም በደል ነፃ ሊያወጣን ይፈልጋል። እያንዳንዱን ነፍስ፥ ሁሉንም ልብ፣ እና የምንኖርበትን ምድር እንኳን መፈወስ እና መመለስ ይፈልጋል። ኢየሱስ ለዚህ 'መቤዠት' እና 'ይቅርታ' መንገድ እንደከፈተ ተነግሮናል። በሚያስደንቅ መንፈሳዊ መንገድ፤ **ኢየሱስ ኃጢአታችንን ወደ ሰውነቱና ሥጋው ወሰደ፣ ከዚያም ከእርሱ ጋር ሞተ።** በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አንድ ጥቅስ፤ 'እርሱ ስለ እኛ ኃጢአት ሆነ' ሲል ይገልጻል።

ኢየሱስ ጥፋታችን እና እፍረታችን ወርሶ ከዚያ ጋር ሞተ። ከኃጢአታችን ጋርም ሞቶ፣ ከዛ ከሞት ተነሳ፣ ነገር ግን ኃጢአታችን ከእርሱ ጋር አልተመለሰም። ኃጢአታችን በመቃብር ውስጥ ትቶታል ማለት ይቻላል። ኢየሱስ ኃጢአታችንን ወሰደ፣ ከእርሱም ጋርም ሞተ፣ ለእኛ ይቅርታን እና አዲስ ሕይወትን ይዞልን ተመለሰ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ኃይለኛ ጥቅስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦ የኢየሱስ ደም ከኃጢአታችን ደም 'የሚበልጥ ቃል ይናገራል'።
በዚህ ምክንያት፣ በኢየሱስ አምነን ይቅርታውን ስንቀበል፣ ለከፈለው የመሥዋዕት ደም፣ 'ለኢየሱስ ደም' አመስጋኞች እንሆናለን።

**በደሙ 'መታጠብ' ትፈልጋላቹሁ?**

## መንፈስ፥

ኢየሱስ ሕያው ነው! ሥጋዊ ነው፤ በሰማይም አለ። አንድ ቀን 'ፊት ለፊት' ልናገኘው እንችላለን።

ነገር ግን ኢየሱስ በቅርቡ ምድርን ትቶ ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው ጊዜ፣ በዚህ ደስ ሊላቸው እንደሚገባ። እንዳታዝኑ ብሎ ነገራቸው። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ወደ እነርሱ መጥቶ ብውስጣቸው ስለሚገባ።

አያቹ፤ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በሰው መልክ ብቻ ነበር። ኢየሱስ በአንድ መንደር ውስጥ ከሆነ በሌላ መንደር አልነበረም ማለት ነው። ኢየሱስ የሰላም እጁን በሰው ላይ እየጫነ እንደሆነ፣ የሰላም እጁን በሌላ ላይ አልጫነም ማለት ነው። እርሱ በሰው መልክ ነበር ስለዚህም ልክ እንደ እኛ በቦታ እና በጊዜ የተገደበ ነበር።

ኢየሱስ ወደ ሰማይ በሄደ ጊዜ፣ ራሱ የኢየሱስ መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በምድር ሁሉ ላይ ፈሰሰ። ይህም ማለት የኢየሱስ ሰው እና ሰላም በእያንዳንዱ መንደር እና በእያንዳንዱ ሰው ልብ እና ቤት ላይ በተመሳሳይ ጊዜ ሊሆን ይችላል ማለት ነው። በተጨማሪም ኢየሱስ በአጠገባችን መሄዱን ብቻ ሳይሆን በውስጣችን መኖር ችሏል ማለት ነው።

አሁን ኢየሱስ በምድር ላይ ተልእኮውን እንዳጠናቀቀ፡- መሞት እና መነሳት ይቅርታ እና የዘላለም ህይወት ሊሰጠን፡- በአካል በሰማይ

ይኖራል። አሁን ከእርሱ ጋር በመንፈስ ቅዱስ እንገናኛለን።

በኢየሱስ ስናምን፤ በመንፈሱ በኩል ወደ እኛ ይመጣል፣ እናም በልባችን፣ በነፍሳችን፣ በመንፈሳችን፡- 'እግዚአብሔር ከእኛ ጋር' ይኖራል።

**በኢየሱስ ማመን እና መንፈስ ቅዱስን በልባቹ እና በህይወታቹ ውስጥ እንዲኖሯቹ ትፈልጋላቹን?**

**መታደም፥**

ኢየሱስ፤ ‵በሩ እኔ ነኝ በእኔም የሚመጣ ሁሉ ይድናል። (ዮሐንስ 10፥9)።

## ኢየሱስን አሁን ወደ ልባቹ እና ወደ ህይወታቹ ልትጋብዙት ትፈልጋላቹን?

ይህ መንፈሳዊ ውሳኔ ነው። ህይወታችሁን ለኢየሱስ ስትሰጡ፣ የኃጢአታችሁ ስርየት እና የዘላለም ህይወት ታገኛላችሁ። ኢየሱስን ባወቃቹበት ቅጽበት በአዲስ መንገድ ላይ ትገኛላቹ፤ እሱም ‵እስከ ቀኑ ብርሃን ድረስ ይበልጥ ብሩህ ይሆናል።' (ምሳሌ 4፥18)።

ከሞት ወደ ሕይወት ድልድዩን እንዴት እንደምንሻገር እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት ማወቅ እንደምንችል እነሆ። 'ማድረግ' የሚገባቹሁ 2 ቁልፍ ነገሮች አሉ። እነዚህን ከዚህ በታች አስቀምጫለሁ፣ እና ከዚያ ልታነቡት እና ከልባችሁ ‘መጸለይ’ የምትችሉትን ጸሎት ጽፌአለሁ፥

1. **ኃጢአት ንስሐ፥**

   ለኃጢአታችሁ ንስሐ መግባት አለባችሁ። አዎ፣ ይህ ከባድ እርምጃ ነው፣ ግን ኢየሱስ የተናገረው አንድ እርምጃ ነው። አሁኑኑ መወሰን አለባቹሁ። በእግዚአብሔር እርዳታ፣ በህይወታቹ ካለው ኃጢአት እንድትርቁ፡- ገንዘብን መውደድ፣ ፍትወት፣

ስግብግብነት፣ ማጭበርበር፤ ሱስ፣ ዝሙት፣ የብልግና ምስሎች፣ ወዘተ።

የኃጢአት ንስሐ 'የልብ ውሳኔ' ነው፤ እና ከጊዜ በኋላ በህይወታቹሁ እና በቤታቹ ውስጥ መታየት አለበት። ለመቁረጥ፣ ለመግባባት፣ ለመጣል፣ ለማጥፋት፣ ለመስጠት የሚያስፈልጋቹ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፥ አሁን ንስሀ ለመግባት ከወሰናቹ እና 'ወደ ክርስቶስ መመለስ' (ይህም 'ንስሃ' ማለት ነው)፤ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እየሄዳቹ ነው፤ በተለይ ለቀጣዩ እርምጃ።

## 2. ብ ኢየሱስ ክርስቶስ ማምን፥

ስለ ሃቅ እና እምነት አስፈላጊነት እና 'ማመን' በማንኛውም እውነተኛ ግንኙነት ላይ ተወያይተናል። ኢየሱስ ‘እርሱን እንድናምን’ ጠርቶናል። ኢየሱስ ይህንን የእምነት እርምጃ እንድንወስድ ጠርቶናል፣ እና በእርሱ ላይ እምነት እንዳለን ጮክ ብላቹ ተናገሩ። የእራሳቹ እምታደርጉት ጸሎት እዚህ ጽፌያለሁ። ጸሎቱ ከልባቹ መነሳት አለበት፤ ቅን መሆን አለባቹሁ።

ለኃጢያታችን ንስሀ ከገባን እና በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንን፣ በዚህ ጊዜ መንፈሱን በልባችን ውስጥ ያደርግዋል፣ ኃጢአታችንም ይቅር ይላል፣ ስማችንም በሰማያት ይጽፍዋል!

## <u>ጸሎት፥</u>

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ስለወደድከኝ አመሰግንሃለሁ። ስለ ኃጢአቴ ስለሞትክ አመሰግንሃለሁ። ይቅርታ እና የዘላለም ህይወት ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ።

ዛሬ ከኃጢአቴ ተጸጽቻለሁ፣ እናም እምነቴን በአንተ ጥያለሁ። ኃጢአቴን ይቅር እንድትልልኝ፣ መንፈስህንም በውስጤ አፍስሰው።

ጌታ ሆይ ይቅር ስላልከኝ አመሰግንሃለሁ። ጌታ ኢየሱስ ሆይ ስላዳንከኝ አመሰግንሃለሁ። ፊት ለፊት እስካይህ ድረስ ታማኝ እንድሆን አሁንኑ እርዳኝ እናም በህይወቴ ዘመን ሁሉ አንተን እንድከተል፣ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ፣ አሜን!

## <u>አዲስ ሕይወት፥</u>

በኢየሱስን መከተል ከወሰዳቹሁ ድናቿል! ይቅር ብሏቿል! እናንተ ‘አዲስ ፍጥረት’ ሆናቿል። ይህ የእግዚአብሔር እውነት ነው። ይህ የኢየሱስ መልእክት ነው።

እንደ ዳግም የተወለደ ‘አማኝ’፣ በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ መጀመር እና ጥቂት ደቂቃዎችን ከኢየሱስ ጋር በጸሎት ማሳለፍ በጣም አስፈላጊ ነው። በእምነታቹሁ እና በሌሎች አማኞች ድጋፍ እንድታድጉ ወደ መልካም የክርስቲያን ቤተክርስቲያን መቀላቀላቹ በጣም አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌላቹሁ እንድትገዙ ወይም እንድትዋሱ ሀሳብ አቀርባለሁ። በኦንላይን ወይም በመጽሐፍት መደብሮች ውስጥ ይፈልጉት።

እኔ የማደርገው በቀን አንድ ምዕራፍ ማንበብ ነው። ምናልባት **በሉቃስ** ወንጌል ይጀምሩ፤ ከዚያ ማንበባቹሁን ቀጥሉ።

ጥሩ እምነት የሚጣልባት ቤተ ክርስቲያን ፈልጉ። በዚህ ውሳኔ እንዲመራቹሁ ጸልዩ፤ ጌታ ኢየሱስንም ለምኑት። ከምታውቁት እና ከምታምኑት ክርስቲያን ስለ ጥሩ ቤተክርስቲያን ምክር ጠይቁ። በሳምንት አንድ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን እና ለጌታ 'መሥዋዕት' መሆኑን ያረጋግጡ። ይህ እንዲሆን በጊዜ መርሐግብራቹ እና በገንዘባቹሁ ውስጥም ቢሆን አንዳንድ ነገሮችን መቀየር ሊኖርባቹ ይችላል። ለዚህ ደግሞ ጌታ ያከብራቿል!

የእናንተን አስተያየት መስማት እወዳለሁ! ይህን የእምነት እርምጃ በድህረ-ገጼ በሚቀጥለው ገጽ አማካኝነት ተቀብላችሁ ከሆነ፣ ኢሜል በመላክ አሳውቁኝ። ከእናንተ ጋር በረከት እካፈላለሁ እና ስለ እናንተም እጸልያለሁ!

ይባርክህ ወንድሜ፤ እህቴ! በአካል እስክንገናኝ ድረስ፣ ሁላችንም ጌታ ቤት ተሰባስበን፤ እግዚአብሔር በኢየሱስ ስም ይባርካቹሁ፣ ይጠብቃቹሁ እና ያበልጽጋቹሁ!

ለተጨማሪ ግብዓቶች፣ እባክዎን ከዚህ በታች ያለውን ድህረ ገፃዩን ይጎብኙ፥

www.1peter1three.weebly.com

**‘ጌታ ይባርካቹ፣ ይጠብቃች፣ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ፣ ይራራላችሁም፣ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ እናንተ መልሶ፣ ሰላምን ይስጣችሁ።’** (ኦሪት ዘኍልቍ 6፥ 24-26።)

የተጠቀሱት ቅዱስ  መጻሕፍት፥

**እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንድንቀርብ ይለምነናል፥** 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥20።

**ክርስቶስን፣ ቅዱሳን መጻሕፍትን፣ መንፈሱን ብቻ ማወቅ፥** 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥2-3።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ተመስጦ እና የተሳሳተ አያያዝ፥** ዕብራውያን፤ 4፥12/ኤርምያስ 29፥13 (በተጨማሪም ማቴዎስ 4፥1-11 እና 2 ቆሮንቶስ 4፥ 2 ይመልከቱ)።

**ያልተማሩ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች፥** የሐዋርያት ሥራ 4፥ 13።

**ኢየሱስ ማለት፤ 'ጌታ ያድናል'፥** ማቴ 1፥21።

**ኢየሱስ እንደ አምላክ በሰው መልክ፥** ኢሳ 7፥ 14/ማቴ 1፥23፣ ኢሳይያስ 9፥6፣ ዮሐንስ 1፥1-5፣9፣14፣ ዮሐንስ 8፥58/ ዘጸአት 3፥ 14፣ ዮሐንስ 10፥30፣ ዮሐንስ 14፥ 9፣ ዮሐ 9፥ 38/ማቴ 14፥ 33/ ኦሪት ዘጸአት 20፥5፣ ዮሐንስ 5፥46፣ ቆላስይስ 1፥15-20፣ ዕብራውያን 1፥3፣ ፊልጵስዩስ 2፥6-11፣ ዘካርያስ 14፥9 / የሐዋርያት ሥራ 4፤12፣ ራእይ 1፤13-18።

**ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ለማለት እና የዘላለም ሕይወትን የመስጠት ዓላማ፥** ሉቃስ 5፥24፣ ዮሐንስ 11፥25-26፣ ዮሐንስ 4፥13-14።

**ራእይ፣ ለመረዳት የማይቻል!፥** ዮሐንስ 6፥37፣ 65፣ ማቴዎስ 16፥16-18፣ ሮሜ 11፥33-36፣ ኢሳይያስ 55፥8-9፣ መዝሙረ ዳዊት 36፤9፣ 2 ቆሮንቶስ 4፥6፣ ዮሐንስ 4፥24 እና ዮሐንስ 6፥ 63።

**በክርስቶስ ማመን፥** ዮሐንስ 7፥37-38፣ ዮሐንስ 11፥25-26፣ ዮሐንስ 9፥35፣ ማቴዎስ 11፥28-30፣ ሉቃስ 5፥24፣ ሉቃስ 10፥20፣ ዮሐንስ 10፥ 9፣ ዮሐንስ 5፥39-40፣ ዮሐንስ 15፥13-15።

**ማየት ማመን አይደለም፥** ዮሐ 11፥45፣ 53፣ ማቴዎስ 26፥56፣ ማርቆስ 15፥25 (9 ጥዋት) ዮሐንስ 20፥29፣ 2 ቆሮንቶስ 4፥6፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥7፣ 1 ዮሐንስ 3፥2፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥12።

**እግዚአብሔር ሁሉንም በእኩልነት ይወዳል፥** 2 ጴጥሮስ 3፥9፣1 ጢሞቴዎስ 2፥4፣ ማቴዎስ 18፥ 14፣ ዮሐንስ 3፥16።

**የክርስቶስን አምልኮ እና የክርስቶስን አለመቀበል፥** ዮሐ 9፥38፣ ማቴዎስ 14:33፣ ዮሐንስ 10፥20፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥16።

**ጥልቅ እና ጸጥ ያለ ራዕይ፥** ማቴዎስ 16፥20፣ ማርቆስ 1፥24፣34፣44፣ ማርቆስ 4፥11፣ ኢሳይያስ 6፥9፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥16፣ መዝሙረ ዳዊት 42፥ 7፣ ማቴዎስ 13፥44።

**ደም እና ነጻነት በክርስቶስ፥ ኢሳያስ፥** 1፥18፣ መዝሙረ ዳዊት 25፥15፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥17፣ ገላትያ 2፥20፣ ሉቃ 4፥18/ ኢሳ 61፥1፣ ኢሳይያስ 42፥3፣ 2 ዜና መዋዕል 7፥14፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥21፣ ዕብራውያን 9፥22፣ ዕብራውያን 12፥24።
መንፈስ፡ ዮሃንስ 14፥1-4፣ ራእይ 1፥13-18፣ 1 ቆሮንቶስ 13፥12፣ ዮሐንስ 14፥17፣26፣28።

**ግብዣ እና አዲስ ሕይወት፥ ኤፌሶን፥** 1፥13-14፣ ቆላስይስ 1፥27፣ ምሳሌ 4፥18፣ ዮሐንስ 5፥24፣ ማርቆስ 1፥15፣ ማቴዎስ 3፥8፣ የሐዋርያት ሥራ 3፥19፣ ሮሜ 10፥9፣ ሉቃስ 10፥20፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥17፣ ዕብራውያን 10፥25፣ መዝሙር 1፣ ኢያሱ 1፥9፣ ዕብ 4፥ 12/2 ጢሞ 3፥16።